## **ሕገ ተዋስቦ**/ ሥርዓተ ጋብቻ

ጋብቻ ምንድነው?

።ጋብቻ አውሰበ፣ ሚስት አገባ፣ተወስበ ተዳረ፣ተዋሰበ ከሚለው የግዕዝ ግስ የተገኘ ቃል ነው። ጋብቻ ለመረዳዳት ለመባዛት ከልዑል እግዚአብሔር ለሰው የተሰጠ ቅዱስ እና ንጹሕ ሕግ ነው።የመሰረተው እግዚአብአሔር ነው። **ሰው ብቻውን ሊኖር አይገባውምና የምትረዳውን እንፍጠርለት** በማለት ለአዳም እና ለሔዋን ባርኮ ቀድሶ ሰጥቷቸዋል። ክርስቲያኖችም እንዲሁ ጋብቻቸውን በቤተ እግዚአብሔር በቅድመ ካህናት **ያስባርካሉ። መጽሐፍ እንዳለ ወንሕነሰ ንብል ከመ ሰብሳብ ንጹሕ ወልደት ዘአልቦ ርኩስ እስመ ፈጠሮሙ እግዚአብሔር ለአዳም ወለሔዋን ከመ ይብዝኁ ሕዝብ** እኛስ ጋብቻ ንጹሕ እንደ ሆነ ልደትም ርኵሰት እንደሌለበት እንናገራለን ሕዝቡ ይበዙ ዘንድ እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን ፈጥሮዋቸዋልና ይላል እግዚያብአሔር አምላክ የመጀመርያውን ሰው ከሕቱም ምድር አበጀው የሕይወትን እስትንፋስ እፍ አለበት ይላል። **ኦዝ መንክር ነሥአ አሐደ አጽመ እምገቦሁ ለአዳም ወለሀኮ እምኔሁ ብሲተ** እንዲል ቅዱስ ኤፍሬም በሚያስደንቅ ርብሩ ከግራ ጎኑም አንዲት አጥንትን በመንሳት ሔዋንን መልከ መልካም ሴት አድርጎ ሰጠው።

መጽሐፍ እንዳለ እግዚአብሔር አምላክም በአዳም ከባድ እንቅልፍን ጣለበት፥ አንቀላፋም፤ ከጎኑም አንዲት አጥንትን ወስዶ ስፍራውን በሥጋ ዘጋው።እግዚአብሔር አምላክም ከአዳም የወሰዳትን አጥንት ሴት አድርጎ ሠራት፤ ወደ አዳምም አመጣት አዳምም አለ፦ይህች አጥንት ከአጥንቴ ናት፥ ሥጋዋም ከሥጋዬ ናት፤ እርስዋ ከወንድ ተገኝታለችና ሴት ትባል።ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፥ በሚስቱም ይጣበቃል፤ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ።ይህም ሥርዓተ ጋብቻ ይባላል። በዚህ አምላካዊ ሕግ መሰረት ሁለት ሁለት ሆነው ለመኖር በጋብቻ ይታሰራሉ። ታዲያ ጋብቻ ትዕዛዘ እግዚአብሔር ከመሆኑ ባሻገር የራሱ የሆነ መንፈሳዊ ሕግጋት አሉት። ክርስቲያኖች ጋብቻቸውን ከመፈጸማቸው በፊት ሙሽሮች ከአበ ነፍሳቸው ጋር ጥልቅ ውይይት ያደርጋሉ። ካህኑም በፈቃደኝነትና ሌላ ሥጋዊ ጥቅምና ፍላጎት አለመኖሩን ያረጋግጣል። በቀኖና መጽሐፍ ተጽፎ እንደምናገኘው **መርዓዊ ወመርዓት ጊዜ ተሐፅዮቶሙ እምቅድመ ይባኡ ውስተ ተዋስቦ መቅድመ ኵሉ ይክሥቱ ፈቃዳቲሆሙ ወእስመ ቦሙ በበይናቲሆሙ ፍቅረ ፍጹመ ለካህን ወካህን ይንግር ለጉባኤ ብእሲ ወብእሲት ወይበል እምቦ እምኔከሙ ዘይክል ያጠይቀነ ከመቦ ምክንያት ዘይከልእ ተዋስቦተ ብእሲ ወብእሲት ይንግረነ ይእዜ እስመ ኢይደሉ ከመ ይትፈለጡ እምድኅረ ተዋሐዱ ወኮኑ አሐደ ሥጋ "ወይንግር ዘንተ ቃለ ለጉባኤ በበእሑድ ሠለስተ ዕለታት እንዲል።** ተጋቢዎቹ ከመጋባታቸው አስቀድሞ ያለ ማንም ተጽዕኖ በራሳቸው ተነሳሽነት ለጋብቻ መዘጋጀታቸውንና በመካከላቸው አማናዊ የሆነ ፍቅር መዋደድ መኖሩን ለካህኑ ይንገሩ። ካህኑም ልጆቻችን እገሌና እገሊት ጋብቻ ለመፈጸም ተፈቃቅደዋል። ከእናንተ ውስጥ የነዚህ ልጆቻችን መጋባት የሚከለክል ምክንያት መኖሩን ሊያስረዳን የሚችል እንዳለ ይንገረን።

በሕጋዊ ጋብቻ አንድ አካል ከሆኑ በኋላ ሊለያዩ አይገባምና በማለት ለተሰበሰበው ጉባኤ እሑድ እሑድ ምዕመናን በሚገኙበት ካህኑ ያውጃሉ። እንደየ ደብሩ አሰራር በማስታወቂያ ቤተክርስቲያን በር ላይም ሊለጠፍ ይችላል። ከሃያ አንድ ቀን በኋላ ሙሽሮቹ ለጋብቻ ይዘጋጃሉ። ይህም ዝግጅት፣ ወንድ ባል ሆኖ ሚስትን ለመቀበልና ለማስተዳደር፣ ሴትም ሚስት ሆና ባልን ለመቀበልና አብሮ ለመኖር ራስን ማዘጋጀት፣ ሁለቱም ያለ ማንም ጣልቃ ገብነትና ግፊት በራስ ተነሳሽነት ኃላፊነትን ለመሸከም ብቁ ሆነው በፍቅር ለመኖር ሥጋዊና መንፈሳዊ ዝግጅት ማድረግ ይኖርባቸዋል። ከተጋቢዎች ዝግጂት በኋላ በመካከላቸው እግዚብሔርን መጋበዝ ይኖርባቸዋል። **ወኵላ ፍድፋዴ እንተ ይገብራ ብእሲ ኢትትፈጸም ዘእንበለ በረድኤተ እግዚአብሔር ወዘእንበሌየሰ ኢትክሉ ገቢረ ወኢምንትኒ** እንዲል።   ማንኛውም ተግባራት ያለ እግዚብሔር   አጋዥነት አይፈጸምምና።

ነቢየ እግዚአብሔር ቅዱስ ዳዊት በሕይወታችን ዘመን ሁሉን ማድረግ የሚችለውን አምላክ ማዕከል አድርገን ማንኛውንም ጉዳያችን በፈቃደ እግዚአብሔር ማከናወን እንዳለብን ይመክረናል። እንዲህ ሲል **እመ እግዚአብሔር ኢሐነጸ ቤተ ከንቶ ይጻምዉ  እለ የሐንጹ እመ እግዚአብሔር ኢዐቀበ  ሀገረ ከንቶ' ይተግሁ  እለ  ይኄልዉ ወከንቱ ገይሥትከሙ ተንሥኡ እምድኅረ ነበርከሙ እለ ትሴሰዩ እክለ ሕማም ሶበ ይሁቦሙ ንዋመ ለፍቁራኒሁ ናሁ ጸጋሁ ለእግዚአብሔር ወሉድ ዕሴተ ፍሬሃ ለከርሥ** እግዚአብሔር ቤትን ካልሠራ፥ ሠራተኞች በከንቱ ይደክማሉ፤ እግዚአብሔር ከተማን ካልጠበቀ፥ ጠባቂ በከንቱ ይተጋል። በማለዳ መገሥገሣችሁም ከንቱ ነው። ለወዳጆቹ እንቅልፍን በሰጠ ጊዜ፥ እናንተ የመከራን እንጀራ የምትበሉ፥ ከተቀመጣችሁበት ተነሡ።እነሆ፥ ልጆች የእግዚአብሔር ስጦታ ናቸው፥ የሆድም ፍሬ የእርሱ ዋጋ ነው። መዝ ፻፳፯፥፩ ( 127፥1) በማለት ሁሉ ከእግዚአብሔር እንደሆነ የመልካም ነገር ሁሉ ምንጭ እሱ እንጂ እሱ ካልሰራ ቤት አይቆምም እሱ ካልጠበቀ አገርም ሰላም አትሆንም። ክርስቲያኖች ሚስት ከማጨታቸው በፊት የሚፈልጓት ሴት ፈሪሀ እግዚአብሔር ያላትና ልጅም ከእግዚአብሔር እንደሆነ የምታምን መሆን አለባት። መጽሐፍ እንደሚነግረን ውበት ሐሰት ነው፥ ደም ግባትም ከንቱ ነው፤ እግዚአብሔርን የምትፈራ ሴት ግን እርስዋ ትመሰገናለች። ምሳሌ ፴፩፥ ፴ አንዳአንድ ሰዎች መልክን፣ውበትን የገቢ መጠንን ወይም ሌላም ሌላም ታሳቢ በማድረግ ለጋብቻ ያጫሉ።

ክርስቲያኖች ግን ይህንን መጸየፍ አለባቸው።ምክንያቱም ሁሉም ያልፋል፣ መልክ ረጋፊ ነው፣ ገንዘብም ጠፊ ነው፣ ጸንተው ሊኖሩ የሚችሉት እምነት፣ ተስፋና ፍቅር ናቸው። የክርስቲያኖች ጋብቻቸው የሚመዘነው በነዚህ ሦስት መሰረታዊ አእማዳት ነው።

ስለዚህ እግዚአብሔር ለባልና ሚስት የሰጣቸው የቤት ሥራ እነዚህን ነው። በተለይ ፍቅር ለባለ ትዳሮች ታላቁ የትዳሩ ምሰሶ ነው። ስለዚህ ባለትዳሮች አማናዊ ፍቅር እንዲኖራቸው ታዘዋል ። ያውም እንዲዋደዱ የታዘዙበት መጠን፣ጌታ ቤተክርስቲያንን በወደደበት ልክ ነው።ኤፌ፳፭፥፳፮  ባልና

ሚስት ሁለታቸው ፍጹም ፍቅር ሊኖራቸው ያስፈልጋል።ሦስተኛው ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው እግዚአብሔርን ጣልቃ ማስገባት ነው። የሚያጸናው እርሱ ነውና። መጽሐፍ እንዳለ  ጠቢቡ ሰሎሞን ስለጋብቻ በተናገረበት አንቀጹ እንዲህ ሲል ተናግሯል።ድካማቸው መልካም ዋጋ አለውና አንድ ብቻ ከመሆን ሁለት መሆን ይሻላል።ቢወድቁ አንዱ ሁለተኛውን ያነሣዋልና፤ አንዱ ብቻውን ሆኖ በወደቀ ጊዜ ግን የሚያነሣው ሁለተኛ የለውምና ወዮለት። ሁለቱም በአንድነት ቢተኙ ይሞቃቸዋል፤ አንድ ብቻውን ግን እንዴት ይሞቀዋል?አንዱም አንዱን ቢያሸንፍ ሁለቱ በፊቱ ይቆማሉ፤ በሦስትም የተገመደ ገመድ ፈጥኖ አይበጠስም። መክብብ ፬፥፱ የብዙ ሰዎች ትዳር ፈጥኖ የሚቆረጠው በሦስት ስለማይገመድ ነው። ሁለታቸው ብቻ ተዋዉቀው ያለበቂ መጠናናትና ፈቃደ እግዚአብሔር ሳይጠየቅ በየቦታው እየተማማሉ በሁለት ይገምዱትና ፈጥኖ ይቆረጣል።

በሦስት የተገመደ ገመድ ግን ፈጥኖ አይቆረጥምና ሦስተኛ እግዚአብሔርን መጋበዝ አለባቸው። ስለዚህ የክርስቲያኖች ጋብቻ በቤተ እግዚያብአሔር ይባረካል፣ ይቀደሳል፣እንዲሁም መጽናትን እና ጸጋ መንፈስ ቅዱስን የሚያሰጥ ስለሆነ መልካም ትዳርና የተባረከ ክርስቲያናዊ ቤተሰብ እንዲፈጠር በሕገ እግዚአብሔር ይከናወናል። ክርስቲያናዊ ጋብቻ ትክክለኛነቱም የሚታወቀው እና የሚረጋገጠው በቤተክርስቲያን በእግዚያብአሔር ፊት ተጋቢዎቹ  ለስርዓተ ጋብቻው ተገዥ ለመሆን፣ በሕጉ ጸንቶ ለመኖር፣ በቤተክርስቲያን በካህናት እና በምዕመናን ፊት በምሐላ ቃላቸውን ሲሰጡ እና ሥጋ ወደሙን ሲፈጽሙ ጋብቻቸው አማናዊ ይሆናል። በጋብቻ ሕግ መጽሐፍ እንደተጻፈው **ማእሰረ ተዋስቦሰ ኢይከውን ወኢይትፌጸም ዘእንበለ በሀልዎተ ካህናት ወጸሎት ዘላዕሌሆሙ ወይመጥውዎሙ ቁርባን ቅዱስ። በጊዜ ተክሊል ዘቦቱ ይትዋሐዱ ክልኤሆሙ። ወይከውኑ አሐደ ስጋ። በከመ ነገረ እግዚእነ ሎቱ ስብሐት  ወዘእንበለ ዝንቱሰ ኢይትኄለቍ ሎሙ አውሰቦ እስመ ጸሎት ይእቲ እንተ ትፌትሕ አንስተ ለእድ፣ ወእደ ለአንስት።**ጋብቻ ካህናት ከሌሉበት ጸሎተ ተክሊል ካልደረሰበት ሊፈጸም አይገባም። ጸሎተ ተክሊል ከተጸለየ በኋላ ሁለቱ አንድ የሚሆኑበትን ቅዱስ ቍርባንን ያቀብሏቸው። ክብር ምስጋና ይግባውና ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስም ባልና ሚስት አንድ አካል ይሆናሉ ብሎ እንደ ተናገረ በሥጋው በደሙ አንድ ይሆናሉ ወንድን ከሴት  ሴትን ከወንድ አንድ የሚያደርጉት ጸሎተ ተክሊልና ቅዱስ ቍርባን ናቸው። እንዲህ ካልሆነ ጋብቻቸው ሕጋዊ አይባልም ተብሎ በመጽሐፍ ተነግሯል። ማቴ:፲፱  ፍትሐ ነገ አንቀጽ ፳፬ ገጽ ፪፻፳፬ እንዲሁም መጽሐፈ ክርስትና ወመጽሐፈ ተክሊል በሚለው መጽሐፍ ላይ ገጽ ፻፵፯ **ወእምቅድመ ኵሉ ይሕትት ካህን ፈቃደ ክልኤሆሙ እለ የኀሥሡ ተዋስቦተ፤ከመ አልቦ ምክንያት ዘይከልአሙ ተዋስቦተ በሕግ፤ ወከመ ቦሙ ስንዑዌ ዘኢያተሉ ተፋልጦተ እስከ ፍጻሜ። ወለእመ ተጠየቀ ሎቱ ከመ አልቦ ምክንያት ዘይከልአሙ እምተዋስቦ፤ወስንዑዊሆሙ ፍጹም በዘይደሉ ያብጽሕ ዘንተ ጸሎተ ዘይተሉ ላዕለ ክልኤሆሙ። ወእምድኅረ ጸሉት ይመጥዎሙ ሥጋሁ ወደሞ ለክርስቶስ እስመ ኢይከውን ተዋስቦቶሙ ለክርስቲያን ፍጹመ ሕጋዌ ዘእንበለ ነሢአ ሥጋሁ ወደሙ ለክርስቶስ።** ካህኑ ከሁሉ አስቀድሞ ለመጋባት

የተፈቃቀዱትን የሁለቱን ሰዎች ጋብቻቸውን የሚከለክል ምክንያት በሕግም ሆነ በሃይማኖት ረገድ፣ እስከ መጨረሻ መለያየትን የሚያስከትል ስምምነት በመካከላቸው አለመኖሩን ይመርምር። እንዲሁም ከመጋባት የሚከለክላቸው ምክንያት አለመኖሩንና ለጋብቻ ያላቸው ስምምነት ፍጹም መሆኑን በሚገባ ከተረዳ በኋላ ጸሎተ ተክሊል ይፈጽምላቸው። ከጸሎቱም በኋላ የክርስቶስን ሥጋውንና ደሙን ያቀብላቸው። የክርስቲያኖች ጋብቻ  ያለ ሥጋ ወደሙ ፍጹም ሕጋዊ ጋብቻ አይሆንምና።ይህ ማለት ስርዓተ ጋብቻ ከቤተክርስቲያን ውጭ አይፈጸምም። ከላይ በመግቢያችን፣ በናንተ ዘንድ ሁሉ በሥርዓት ይሁን እንዳልነው፣ የክርስቲያኖች ጋብቻበሰፈር፣ በመንደር፣ በባህል አይፈጸምም።ቤተክርስቲያኗ ለዚህ ያዘጋጀችው መመሪያ በቤተክርስቲያን ብቻ እንዲፈጸም ስለሚያዝ ነው። ሌላው ስለጋብቻ በትዉፊት እና በመጽሐፍ ቅዱስ ሲታይ መንገዳቸውን ከእግዚአብአሔር ጋር ያደረጉ ቅዱሳን፣ አምላካቸውን ካስደሰቱበት መንገድ አንዱ፣ በጋብቻቸው ታማኝነት ነበር። ከእነሱም  በቅድስናቸው ከተመሰከረላቸው ብዙ ቅዱሳን ለምሳሌ አብርሃም ይስሓቅ ያዕቆብ፣ ዘካርያስ ጸጋ ዘአብና ሌሎችንም መጥቀስ ይቻላል። በተለይ አብርሃም ከሣራ ጋር በነበረው የትዳር መልካም ኑሮ ለክርስቲያኖች ትልቅ ምሳሌ በመሆኑ ለጋብቻ የመልካም ምኞት መገለጫ ሆኖ ሲያገለግል ይኖራል። አብርሃም ልጅ ባለማግኘቱ በትዳሩ ተፈትኗል። ነገር ግን ለትዳሩ ባለው መንፈሳዊ አክብሮት ጌታዬና እመቤቴ እየተባባሉ ኖረዋል።ባል በገዛ ሥጋው ላይ ሥልጣን የለውም፥ ሥልጣን ለሚስቱ ነው እንጂ። በሚለውን መሰረታዊ ትዕዛዝ አብርሃም ወደ አጋር የመግባት ስልጣን እንደሌለው የተረዳችው ሣራ ከሰራተኛዋ በመድረስ ዘር እንዲተካ አዘዘችው። አብርሃምም ወደ አጋር ገባ ፀነሰችም። አጋርም በናቀቻት ጊዜ አብርሃም ባሪያሽ በእጅሽ ናት የወደድሽውን አድርጊ አላት። አጋርም ኮበለለች አብርሃም አጋር ስላረገዘች ለሚስቱ ለሣራ የተለየ አመለካከት አልነበረውም። ይልቁን አብልጦ ይወዳት ነበር እንጂ። ፩ኛ ቆሮንቶስ ፯፥፬ ዘፍ ፲፮፥፫ የአብርሃም የልጅ ልጅ የሆነው ሕዝበ እግዚአብአሔር የተባለው እስራኤል ራሔልን ለማግባት ለላባ አስራ አራት ዓመት አገልግሏል። ታሪኩን በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተመዘገበው ያዕቆብም ስለ ራሔል ሰባት ዓመት ተገዛ፤ እርስዋንም ይወድዳት ስለነበረ በእርሱ ዘንድ እንደ ጥቂት ቀን ሆነለት። በነጋም ጊዜ እነሆ ልያ ሆና ተገኘች፤ ላባንም፡- ምነው እንደዚህ አደረግህብኝ? ያገለገልሁህ ስለ ራሔል አልነበረምን? ለምን አታለልኸኝ? አለው። ይህችንም ሳምንት ፈጽም፤ ሌላ ሰባት ዓመት ደግሞ እኔን ስለምታገለግለኝ አገልግሎት እርስዋን ደግሞ እሰጥሃለሁ አለው። ዘፍ ፳፱፥፳–፳፰ ያዕቆብም ለራሔል ጽኑዕ የሆነ አማናዊ ፍቅር ስለነበረው አስራ አራት ዓመት ለላባ ተገዝቷል። የአሁኑ ትውልድ እንኳን እራሱን ሊሰጥ ይቅርና አንዲት የአንገት ሐብል ለመግዛት ምን ያህል እንደሚከብደው ሁላችንም እናውቀዋለን። እንግዲህ በዚህ እርዕስ የጋብቻ ክፍሎችና ሕጎችን እናያለን። ሐዋርያው ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ምዕመናን በጻፈላቸው መልእክቱ በእናንተ ዘንድ ሁሉ በስርዓት ይሁን ይላል። ፩ቆሮንቶስ ፲፬፡-፵ ይህንንም መሰረት በማድረግ ስለ ስርዓተ ጋብቻ የራሱ የሆነ መንፈሳዊ ሕገ ደንብ አለው። በመሆኑም  ሊቃውንት አባቶቻችን እንዳስተማሩን ሥርዓተ ጋብቻ **በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላል።** ይህ ማለት ግን ሁለት አይነት

ጋብቻ ወይም ሁለት ጊዜ የሚፈጸም ጋብቻ ኖሮ ሳይሆን በቤተ ክርስቲያን ጋብቻቸውን የሚፈጽሙ ምዕመናን በሁለት መንገድ እንዲያከናውኑ ለማሳሰብ ነው።

**፩ ተክሊል**

**፪ መዓስብ**

ተክሊል

ተክሊል ማለት ከለለ አከበረ ከሚለው የግዕዝ ግስ የተገኘ ሲሆን ተክሊል መቀዳጀት፣ማስጌጥ፣ መሸለም፣ለንጉሥና ለሙሽራ ዘውድ መድፋት ተብሎ ይተረጎማል። አማኞች ቅድመ ሥርዓተ ጋብቻ በመተጫጨት እና በመጠናናት በእውነተኛ ፍቅር የተመሰረተ ግንኙነት ወይም መተዋወቅ ሊኖራቸው ያስፈልጋል። በተጋቢዎቹ መካከል ለጋብቻው እንቅፋት ሊሆን ይችላል የተባሉትን በሙሉ በማስወገድ፣ ተጋቢዎቹ በሚገባ ከተጠናኑ እና ከተዋወቁ በኋላ ለአበ ነፍሳቸው በመንገር ሱባኤ ይዘው እግዚአብሔርን በጸሎት ይጠይቃሉ። ትዳር ከእግዚአብአሔር የሚሰጥ ነውና በቤተክርስቲያን ቀርበው ጋብቻቸውን ይፈጽማሉ። **የምሥጢረ ተክሊል** አተገባበሩ እንደሚከተለው ነው። ሙሽሮች በንስሐ አባቶች እና በወላጆች የሃይማኖት እና የባህል ዘይቤያቸው በሚገባ ከተጠና እና ለመለያየት ምክንያት የሚሆንባቸው ነገር አለመኖሩን በማረጋገጥ በሱባኤ ከታየ እና ክብረ ንጽህናቸው፣ በድንግልና መጽናታቸው ከተረጋገጠ በኋላ ተክሊል ይፈጸምላቸዋል። ለዚሁም ክብረ ንጽህናቸውን ጠብቀው በመቆየታቸው ነጭ ካባ ይለብሳሉ። ክብረ ድንግልናቸዉን ጠብቀው ስለቆዩ፣ ከቡራን ናቸውና ነጭ አክሊል ይቀዳጃሉ ወይም ይደረግላቸዋል። ተክሊል በድንግልና ለጸኑ ብቻ ይፈጸማል።ተጋቢዎችን አንድ የሚያደርጋቸው ሥጋ ወደሙ ሲሆን ተክሊል ግን ከላይ በመግቢያችን እንዳልነው ሽልማት ነው። በጽናት ንጽሕናውን ጠብቆ በመቆየቱ ወይም በመቆየቷ የሚሰጥ እውቅና ነው። ይኸውም የሰማያዊ አክሊል ምሳሌ ነው። ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ እንዳለው መልካሙን ገድል ተጋድዬአለሁ፥ ሩጫውን ጨርሼአለሁ፥ ሃይማኖትን ጠብቄአለሁ፤ ወደ ፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል፥፪ኛጢሞ፬፥፯ በመሆኑም ኦርቶዶክሳዊት ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያናችን እስከ ጋብቻ ድረስ በንጽሕና በድንግልና ለጸኑት ልጆቿ የምታቀዳጀው አክሊል የዚህ ምሳሌ ነው። ከመካከላቸው አንደኛው በድንግልና ባይገኝ፣ በድንግልና ጸንቶ የተገኘው አካል ሥርዓተ ተክሊል ይፈጸምለታል(አክሊል ይቀዳጃል)። ጸሎተ ተክሊል የተባለው መጽሐፍ ይጸለይላቸዋል በወላጆቻቸው እና በቅርብ ዘመዶቻቸው መካከል በዕለቱ በቤተ መቅደስ ስርዓተ ተክሊላቸው ከተደረሰላቸው በኋላ ከላይ እንደጠቀስነው ቅዱስ ቁርባን ይቀበሉና ስርዓቱ ይፈጸማል። ከዚህ ላይ መታለፍ የሌለበት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን አማኞች ዘንድ አገልጋዮች እንኳ ሳይቀሩ የሚወድቁበት ፈተና አለ።እርሱም ከቆረቡና ከተባረኩ በኋላ እንደ ገና መራቆት ነው። ጧት ቤተክርስቲያን ቆርበው ማታ ዓለማዊ ልብስ ለብሰው የተለያየ ቦታ የፎቶ መርሐ ግብር እያሉ ሥርዓት የሚያፈርሱ አሉ። አንባቢ ሆይ በሃይማኖት ብትኖሩ ራሳችሁን መርምሩ፤ ራሳችሁን ፈትኑ፤ ወይስ ምናልባት የማትበቁ ባትሆኑ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ በእናንተ ውስጥ እንዳለ ስለ እናንተ አታውቁምን? ፪ኛ ቆሮ ፲፫፥፭ ለመሆኑ ለፎቶ ብሎ መራቆትህ ወይም መራቆትሽ ከለበስከው ሱፍ የቆረብክበት ካባ ምን ያህል ክብር እንዳለው አታውቅምን? ክርስትና ሁሉም አይቅርብኝ ተብሎ ይቻላልን? መንፈሳዊነትም ፈልጋችሁ፣ ዓለማዊም ፈልጋችሁ እንዴት ይሆናል? ታድያ ምን ላይ ነው ከዓለም የተለየነው? እስከመቼ ለብ ብለን እንኖራለን? ሃይማኖተኛ ከሆናችሁ የሃይማኖት ሥራ መሥራት እንጂ መቀላቀል ለመንፈሳዊ ሕይወት አይበጅም። መጽሐፍ እንዲህ ይላል።ከማያምኑ ጋር በማይመች አካሄድ አትጠመዱ፤ ጽድቅ ከዓመፅ ጋር ምን ተካፋይነት አለውና? ብርሃንም ከጨለማ ጋር ምን ኅብረት አለው ክርስቶስ ከቤልሆር ጋር

ምን መስማማት አለው? ወይስ የሚያምን ከማያምን ጋር ምን ክፍል አለው? ፪ ቆሮ ፮፥፲፬ ክቡራን አንባቢዎች ሆይ መልክቱ ላያስደስታችሁ ይችላል ነገር ግን ጥሬና ብስል ሆኖ፣ ከአንገት በላይ ታቦት ከአንገት በታች ጣኦት ሆኖ መኖር ፈጽሞ የማይመች አካሄድ ነው። ክርስቲያኖች መልካም ሥራችሁ በሰው ፊት ይብራ መታወቂያችን በጎ ስራችን፣ሃይማኖታዊ ምግባራችን ነው። ክርስቲያናዊ አለባበስ ፈልገን ካባ ለብሰን፣ ከቆረብን በኋላ ዓለማዊ ልብስ ቬሎ እየፈለግን ሁለት ልብ ሆኖ ክርስቶስን መከተል አይቻልም። ይህንንም ጌታ ክርስቶስ አስተምሮታል አንድ ደቀ መዝሙር የነፍሱ ጉዳይ አሳስቦት ሊከተለው ፈለገ ነገር ግን የቤተሰቦቹ ጉዳይም አሳሰበው ጌታም አንዱን መተው አለብህ ሲለው እናያለን። ቃሉ እንዲህ ይላል፣ ሌላውም ተከተለኝ አለው። እርሱ ግን፦ ጌታ ሆይ፥ አስቀድሜ ልሂድና አባቴን እቀብር ዘንድ ፍቀድልኝ አለ።ኢየሱስም፦ ሙታናቸውን እንዲቀብሩ ሙታንን ተዋቸው፤ አንተስ ሄደህ የእግዚአብሔርን መንግሥት ስበክ አለው።ደግሞ ሌላው፦ ጌታ ሆይ፥ እከተልሃለሁ፤ ነገር ግን አስቀድሜ ከቤተሰቦቼ እንድሰናበት ፍቀድልኝ አለ።ኢየሱስ ግን፦ ማንም ዕርፍ በእጁ ይዞ ወደ ኋላ የሚመለከት ለእግዚአብሔር መንግሥት የተገባ አይደለም አለው። ሉቃ ፱፥፶፱ ስለዚህ አንድ አማኝ እራሱን ለክርስቶስ ከሰጠና በሃይማኖት ካለ የዓለም አለባበስ፣አመጋገብና ኑሮ ሊያሳሳው ወይም ሊናፍቀው አይገባም። በተለይ ቅዱስ ዮሐንስ በመልእክቱ እንዲህ ሲል ጽፏል **አ አኃውየ ኢታፍቅርዎ ለዓለም ወኢዘሀሎ ውስተ ዓለም ዓለሙኒ ኃላፊ ፍትወቱኒ ኃላፊ እስመ ኩሉ ኃላፊ ውእቱ**/ዓለምን ወይም በዓለም ያሉትን አትውደዱ፤ በዓለም ያለው ሁሉ እርሱም የሥጋ ምኞትና የዓይን አምሮት ስለ ገንዘብም መመካት ከዓለም ስለ ሆነ እንጂ ከአባት ስላልሆነ፥ ማንም ዓለምን ቢወድ የአባት ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለም።ዓለሙም ምኞቱም ያልፋሉ፤ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርግ ግን ለዘላለም ይኖራል።፩ዮሐ ፪፥፲፳ **ኃላፊ ጠፊውን** ዓለምን ክዶ ወደጌታው የመጣ አማኝ በቤቱ ያገኘውን፣ በቤቱ የተሰጠውን ከለበሰ ሌላ አያስፈልገውም።ክርስቲያኖች ወደ ነፍሳቸው እረኛ ወደ እግዚአብሔር ከተመለሱ ከተባረኩ፣ከቆረቡ፣ከተቀደሱ በኋላ የዓለም የሆነ ሁሉ ሊያምራቸው አይገባም።በመሆኑም ጋብቻቸውን በተክሊልም ይሁን በመዓስብ በሁለቱም መንገድ የሚፈጽሙ ክርስቲያኖች ዕለቱን በቆረቡበት በመንፈስ ቅዱስ በከበሩበት ልብሰ መራዊ ወመራት( የሙሽራ ልብስ) እንደለበሱ ይውላሉ እንጂ በዚያው ዕለት መራቆት ተገቢ አለመሆኑን ለማስገንዘብ እወዳለሁ።

## ፪ <u>መዓስብ</u>

መዓስብ ዐሰበ ፈት ኾነ፣ ገለሞተ ብቸኛ ሆነ የሚል የግስ ፍች ያለው ሲሆን መዐስባን በሞት ወይም በተለያዩ ነውር ምክንያቶች ትዳር አልባ የሆኑ መበለቶች ማለት ነው። ለነዚህ የሚደረገው የጋብቻ አይነት ሥርዓተ መዓስባን ይባላል። የመዐስባን ጋብቻ የሚፈጸምላቸው ምዕመናን በሁለት ምክንያቶች ነው።

**፩ኛ** ፣ጋብቻቸውን በሥርዓተ ተክሊል ፈጽመው ኖሮ፣ ከጥንዶቹ አንደኛው በሞት ቢለይ በሕይወት ያለው አካል ቀሪ ዘመኑን በጽናት መኖር የማይችል ከሆነና ሌላ ማግባት ቢፈልግ ወይም ብትፈልግ፣ የመዓስባን ጋብቻ ይፈጸምላቸዋል።

**፪ኛ** በተለያየ ምክንያት ድንግልናቸውን ያጡ በንስሐ የተመለሱ ለነዚህ ጥቁር ወይም ቀይ ልብስ ቤተክርስቲያኗ እንዳዘጋጀቺው የሙሽራ ልብስ ይለብሳሉ። ከመጽሐፈ ተክሊልሉ የሚገባቸውን ጸሎተ መዓስብ የተባለው የጸሎት ክፍል ይደርስላቸውና ይቆርባሉ።

ባልና ሚስት ከተጋቡ በኋላ አንድ አካል ናቸው እንጂ ሁለት አይደሉም። በዚህ ምክንያት ወንዱ አባቱንና እናቱን ትቶ ከሚስቱ ጋር ይዋሃዳል። ሴቲቱም እናት አባቷን ትታ ከባሏ ጋር ትዋሃዳለች ይህም አንድ ይሆናሉ በሚለው አምላካዊ ቃል መሰረት ከላይ እንደተባለው አንድ የሚያደርጋቸው ቅዱስ ቁርባን ነው። ሁለቱ አንድ ይሆናሉ ማለት የባሏ የሆነ ሁሉ የሷ ነው። የሚስቱ የሆነ ሁሉ የሱ ነው። ይህ ማለት ባልም ሆነ ሚስት የኛ እንጂ የኔ የሚሉት የብቻ የሆነ ነገር ሊኖር አይገባም። አንዳአንድ ሰዎች ከሚስታቸው ደብቀው ሐብት ንብረት ያካብታሉ።

በተለይ በውጭ ሀገር በስደት የሚኖሩ ባለ ትዳሮች ከሚፈተኑበት አንዱ ሳያሳውቁ ትዳራቸውን ደብቀው ገንዘብ ለቤተሰብ መላክ ነው። ይህ ነውር ነው። ለእርዳታ መላኩ በጎ ሳለ ሁለቱም አምነዉበት ተመካክረው መሆን አለበት። ምክንያቱም የሚስቱ ዘመድ የሱ ዘመድ ነው። የባሏ ዘመድ የሷም ዘመድ ነውና። ምስጢርን ከትዳር ጓደኛ መደበቅ የትዳር ጠንቅ ነው። በመካከላቸው እውነት ጠፍቶ አታላይነትና መደባበቅ እንዲሁም ውሸት መናገር በትዳር ውስጥ ትልቅ ፈተና ነው። የሐሳብ መለያየት ሲኖር ትዳሩም አይጸናም። ጌታ በወንጌል እንዳለ እርስ በርስዋ የምትለያይ መንግሥት አትጸናም፣ ትጠፋለች፥ እርስ በርሱ የሚለያይ ከተማም ሁሉ ወይም ቤት አይቆምም ይላል። ማቴ ፲፱፥ ፭፮ ትዳር የሚቆመው በሆደ ሰፊነት፣ በይቅርባይነት፣ ከሁሉም በላይ ሁለቱም ለትዳራቸው ዋጋ መክፈል የሚችሉበት ቁመና ሲኖራቸው ነው።

አንድ አንዱ ሚስት አግብቼ በምን አስተዳድራታለሁ ? ምን ላበላት፣ ምንስ ላጠጣት ? የሚሉ ከንቱ ሐሳቦችን እንደ ምክንያት ሲያነሱ እናያለን። እንዲህ አይነት ሰዎች ሃይማኖት የሌላቸው ናቸው። ሰውን የሚያኖረው እግዚአብሔር ነው። እኛ እየኖርን ያለነው ስለበላን፣ስለጠጣን አይደለም። እግዚአብሔር ስለፈቀደ ብቻ ነው እንጂ። የሚያኖር፣የሚመግብ እግዚአብሔር ነው። ቅዱስ ዳዊት **አነ ውእቱ አምላክከ ዘአውጻእኩከ እምግብፅ አርህብ አፉከ ወእመልአ ለከ** ከግብጽ ምድር ያወጣሁህ እኔ እግዚአብሔር አምላክህ ነኝና፤ አፍህን አስፋ እሞላዋለሁም።መዝ ፹፩፥፲ በማለት የሚሞላ፣ የሚያጠግብ እግዚአብሔር እንጂ ሰው ስለሮጠና ስለቀደመ የሚሆን ነገር አለመኖሩን እስራኤላውያን በበረኃ ያኖራቸውን አምላክ ጠቅሶ ተናግሮታል። እንደውም ሚስት ያገባ በረከት አገኘ ተብሎ ነው በመጽሐፍ የተጻፈው። ሚስት ያገኘ በረከትን አገኘ፥ ከእግዚአብሔርም ሞገስን ይቀበላል።ምሳሌ ፲፰፥ ፳፪ ቅድስት ሥላሴ የምትረዳው እንፍጠርለት **የምትረዳው**። ይህን ውጣውረድ የበዛበት ዓለም የምታግዝ ትዳሯን የምታከብር ሚስት በረከት ናት። በመካከላቸው የኔ ይቅርብኝ ለአንተ ይሁን፣ አንቺ ትብሻለሽ ለአንቺ ይሁን፣ የሚል የመተሳሰብ ተግባር በመካከላቸው ሊኖር ይገባል። ትዳርን መምራት

ቤተሰብን ማስተዳደር ሀገር ከመምራት አይተናነስም። በሁለቱም በኩል ከራስ ይልቅ ለሌላው ማሰብ በእግዚአብሔርም በሰው ዘንድም ውጤታማነት አለው አንድ አንድ መሪዎች የሚመሩትን ሕዝብ ሰርቀው በውጭ ሀገር ባንክ ገንዘብ ሲያስቀምጡ፣ ሲዋሹ ለእግዚአብሔርም ለሕዝባቸውም ሳይመቹ ያልፋሉ መልካም መሪዎች ሟች መሆናቸውን ተረድተው ሕዝባቸውን በቅንነት አገልግለው ተባርከው በታሪክ በመልካም ሲዘከሩ ይኖራሉ። ትዳርም እንዲሁ ነው።በታማኝነት በመንፈሳዊነት፣ በሕገ እግዚአብሔር ከተመሩ በዚች ምድርም በሰላም ከመኖር አልፎ በሰማይም መልካም ዋጋ ያለው በመሆኑ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው። ትዳር የዚህን ዓለም ኑሮ እንኳን ለማቅለል  ትልቅ ፋይዳ አለው። ከላይ እንዳልነው በትዳር ውስጥ እራስ ወዳድነት አያስፈልግም። ከላይ እንደገለጥነው አንዱ ለሌላው ማሰብ፣ሰጭ መሆን መጽሐፍ እንዳለ ከሚቀበል ይልቅ የሚሰጥ ብፁዕ ነው እንዳለ የጌታን የኢየሱስን ቃል ልታስቡ ይገባችሁ ዘንድ በሁሉ አሳየኋችሁ። ሐዋ ፫፥፳፰  በማለት ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ ለደቀ መዛሙርቱ እንዳስተማረው በትዳር ውስጥ ከመቀበል ይልቅ ሰጭ መሆን ጠቃሚ ይሆናል። በተለይ ሴቶች ስጦታን ይወዳሉና። ስጦታ አክብሮት ከሚገለጥበት  መንገድ አንዱ ነውና ይህ አይነት መከባበር የሰፈነበት ትዳር ውጤቱ ያማረ ነው።መንፈሳዊና የተባረከ ቤተሰብ የሚወጣው እግዚአብሔርን ከሚፈራ ቤተሰብ ነው። መልካም ዛፍ መልካም ፍሬ ይሰጣልና መጽሐፍ **እንዳለ  ብዕሲትከ ከመ ወይን ስሙር ውስተ ጽርሐ ቤትከ ወውሉድከ ከመተክለ ዘይት ሐዲስ አውደ ማዕድከ** ሚስትህ በቤትህ እልፍኝ ውስጥ እንደሚያፈራ ወይን ናት፤ ልጆችህ በማዕድህ ዙሪያ እንደ ወይራ ቡቃያ ናቸው። መዝ  ፻፳፰፥፫ (128፥3)

## <u>አጠቃላይ የክርስቲያኖች የስርዓተ ጋብቻ መመሪያ ደንብ</u>

ይህ ንዑስ እርዕስ ማንኛውም ሰው ስለ ጋብቻ ከእግዚአብሔር የተሰጠውን ቋሚ ሕግ አውቆ መመሪያቸው አድርገው ተጋቢዎች ለትዳራቸው ተገቢውን ክብር መስጠት እንዲችሉ የሚመራ ነው። ሰዎች ጋብቻ የፈቃድ መስሏቸው ሲጋቡ ሲፋቱ እንዳይኖሩ፣ የቤተክርስቲያኗ አማኞች በግድ ሊጠብቁት የሚገባ ሕግ ነው። በእግዚአብሔር አጋዥነት በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው አባቶቻችን ሐዋርያት ሊቃውንት የሰሩልን የማይሻር ሕግ መኖሩን እንድንገነዘብ የተዘጋጀ አስራ ሁለት ዋና ዋና ነጥቦች ያሉት ከብሉይ እና ከሐዲስ እንዲሁም ከፍትሐ ነገስት የተወሰዱ የጋብቻ ሕጎች አሉ። እነዚህ የስርዓተ ጋብቻ መመርያ ሕጎች እንደሚከተለው በዝርዝር ቀርበዋል።

**፩ኛ** በስርዓተ ተክሊል ለሚጋቡ፣ ወንድ ከ ፲፰ ዓመት በላይ ሴት ከ፲፰ዓመት በላይ ሲሆኑ አምነውበት፣ ያለ ማንም ጣልቃ ገብነት፣ መፈቃቀዳቸውንና ተዋደውና ተፋቅረው ሲቀርቡ ተጋቢዎቹ በሚኖሩበት አጥቢያ ጋብቻ የሚፈጽሙት ሙሽሮች ከመፈጸማቸው በፊት በአጥቢያው አዋጅ ይነገራል። ጥቅምን ያላማከለ አማናዊ መተጫጨት መሆኑን አስተያየት ካለና የቀረበው አስተያየትም

ከቅንነት የመነጨ መሆኑ ይመረመራል። ጋብቻው በሁለታቸው መዋደድ ላይ ይመሰረታል። መጽሐፍ እንዳለ ስለዚህ ወንድ አባቱንና እናቱን ይተዋል ሚስቱንም ይከተላል። ዘፍ ፪:-፳፫ ማቴ ፲፱:፭

**፪ኛ** በሁለተኛ ደረጃ ከዕድሜ ገደብ ቀጥሎ ሊታወቅ የሚገባው ተጋቢዎች ስለ ጋብቻ ክብርና ስለሚቀጥለው በትዳር የመኖር ጊዜ የሚያትት፣ ጋብቻ ምን ያህል ክቡር እንደሆነ ግንዛቤ እንዲኖራቸው፣ በንስሐ አባታቸው ሰፊ ግንዛቤ የሚሰጥ ትምህርት ለተጋቢዎች ይሰጣል። መጽሐፍ እንዳለ ጋብቻ በሁሉ ዘንድ ክቡር መኝታውም ንጹሕ ይሁን፤ ሴሰኞችንና አመንዝሮችን ግን እግዚአብሔር ይፈርድባቸዋል።"ዕብራውያን ፲፫:-፬ ማንኛውም አማኝ ጋብቻ ከመፈጸሙ በፊት ስለ ጋብቻ በቂ ግንዛቤ ሊኖረው ይገባል። ምክንያቱም ሰርግ ተበድሮም ማስረግ ይቻላል። በትዳር ውስጥ የሚገጥሙትን ፈተናዎች ግን ተቋቁሞ ማለፍ ቀላል አይደለምና በመሆኑም ሁለተኛው የጋብቻ ዝግጅት ስለ ጋብቻ በቂ ትምሕርት ማግኘት ነው።

**፫ኛ** ባልና ሚስት ከተጋቡ በኋላ መፋታት አይፈቀድም።ባልና ሚስት በልዩ ልዩ ዓለማዊ ምክንያት መፋታት ቃል ኪዳናቸውን ማፍረስ አይገባቸውም ሴት ከባሏ አትለይ ወንድም ከሚስቱ አይለይ ፤ ሁላችሁም በጌታችን ትእዛዝ አንድ ሆናችኋልና ስለዚህ ባልና ሚስት በአንድ ላይ ቃላቸውን አጽንተው መኖር አለባቸው። መጽሐፍ እንዳለ እናንተም፦ ስለ ምንድን ነው? ብላችኋል። ሚስትህ ባልንጀራህና የቃል ኪዳንህ ሚስት ሆና ሳለች እርስዋን አታልለሃታልና እግዚአብሔር በአንተና በልጅነት ሚስትህ መካከል ምስክር ስለሆነ ነው። እንዲሁም ጌታም በወንጌል እንደተናገረ እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን ሰው ሊለይ አይችልም። በቅዱስ ቁርባን አንድ ስለሆኑ በፍጹም መለያየት የለባቸውም። ፩ቆሮ ፲፩፥ ፲፩ ማር ፲:፪-፱ ሚልክ ፪ ፦፲፬-፲፯ ኤፌሶን ፭፥፴፩

**፬ኛ** ጋብቻ አንድ በአንድ ይጸናል እንጂ ሁለተኛ ቁጥርን አይነካም። ይህም ማለት ለአንድ ወንድ አንዲት ሴት፣ ለአንዲት ሴት አንድ ወንድ፣ እንጂ ለአንድ ወንድ ሁለት ሴት፣ ወይም ለአንዲት ሴት ሁለት ወንድ አልተፈቀደም። ተፈጥሮም የሚያስተምረው ይህንኑ ነው። ለአንድ አዳም አንዲት ሔዋን ተሰጥታዋለችና። ባል ከሚስቱ ሚስትም ከባሏ መተላለፍ የለባቸውም። ባል በሚስቱ ብቻ ሚስትም በባሏ ብቻ ተወስነው ይኖራሉ እንጂ። መጽሐፍ እንዳለ እንዳትሰስኑ ሰው ሁሉ በሚስቱ ጸንቶ ይኑር ሚስትም በባሏ ጸንታ ትኑር። ፩ቆሮ ፯፥፪

**፭ኛ** አምስተኛው መመሪያ ፍላጎትን ማሟላት በተመለከተ ነው።ባል ለሚስቱ፣ሚስትም ለባሏ እንድታደርግለት ወይም እንዲያደርግላት የሚገባትን ሁሉ መጠበቅ ማድረግ ይገባዋል። ስጦታ መስጠት ሊሆን ይችላል፣በማሕበራዊ ኑሮ ውስጥ እንዳያደርግ የምትፈልገው ነገር ሊኖር ይችላል፣ በአጠቃላይ ባል ለሚስቱ ማድረግ እስከቻለ ድረስ የምትፈልገውን ሁሉ ማድረግ አለበት።ሴትም ለባሏ የሚገባውን ማድረግና መጠበቅ ይገባታል።ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ እንዳለው ወንድ ለሚስቱ የሚገባትን ያድርግላት ሴትም ለባሏ የሚገባውን ታድርግለት።፩ ቆሮ ፯:፫

**፮ኛ** ሴት ባሏ ያዘዛትን ልትፈጽም እንጅ በባሏ ላይ የሌላ ትዕዛዝ ፈጻሚ ልትሆን የወደደችውን ልታደርግ በራሷ ላይ ስልጣን የላትም በእሷ ላይ የማዘዝ ስልጣን ያለው ባሏ ብቻ ነው። እንዲሁም ወንድ በሚስቱ ላይ የሌላይቱ ታዛዥ ሊሆን የሌላይቱንም ፈቃድ ሊፈጽም በራሱ የማዘዝ ስልጣን የለውም።በእሱ ላይ ስልጣን ያላት የምታዝዝበት ሚስቱ ናትና።ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ በመልእክቱ ሴት በራሷ ስልጣን የላትም ስልጣን ለባሏ ነው እንጂ። እንዲሁም ወንድ በራሱ ላይ ስልጣን የለውም። ስልጣን የሚስቱ ነው እንጂ ፩ ቆሮ ፲፩፡ ፬።

**፯ኛ** ይህም ሕግ የባለ ትዳሮችን አብሮነት የሚያጠናክር ሕግ ነው።ለጾምና ለጸሎት ከተወሰነ ቦታና ጊዜ በቀር ባልና ሚስት መለያየት የለባቸውም። ሰይጣን ድል እንዳይነሳቸው ተጠባብቀው መኖር ይገባቸዋል። መጽሐፍ እንዳለ ለጸሎት ትተጉ ዘንድ ተስማምታችሁ ለጊዜው ካልሆነ በቀር፥ እርስ በርሳችሁ አትከላከሉ። ራሳችሁን ስለአለመግዛት ሰይጣን እንዳይፈታተናችሁ ደግሞ አብራችሁ ሁኑ ፩ ቆሮ ፯፥፭። ጾምም ጸሎትም ተስማምቶ እንጂ አንዱ ስለፈለገ ሌላኛው ካልፈለገ ተፈጻሚነት አይኖረውም። ለዚህ ነው ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ **<ተስማምታችሁ ለጊዜው ካልሆነ በቀር፥ እርስ በርሳችሁ አትከላከሉ>** ሲል ባለትዳሮች በተለያየ ቦታ መኖር እንኳ እንደሌለባቸው ያመለክታል።

**፰ኛ** ይህ መመሪያ ሚስቶች ለባሎቻቸው መታዘዝ እንዳለባቸው የሚያስረዳ.ነው።ቤተክርስቲያን ለክርስቶስ እንደምትታዘዝ ሚስትም አሳዳሪዋ ስለሆነ ለባሏ መታዘዝ ይኖርባታል። እንዲሁም ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን እንደወደዳት እራሱንም ለሞት አሳልፎ እንደሰጠላት ስጋውን ደሙን እንደመገባት እንዲሁም ወንድ አካሉ ናትና ሚስቱን መውደድ መርዳት ይገባዋል።ኤፌ ፭፥፳፪-፴፫ ይህን የተናገረው ሐዋርያው ጳውሎስ ነው። ባልና ሚስት ሊፋቀሩበት የሚገባውን መጠን ሲያስቀምጥ፣ የክርስቶስንና ለቤተክርስቲያን የከፈለውን መስዋዕትነት በማውሳት በዚያ ልክ ባል ሚስቱን መውደድ አለበት። ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን የወደደበት መጠን ስንመለከት እስከ ሞት ድረስ ነው። በዚህ ልክ ባልና ሚስት መዋደድ አለባቸውም። እስከሞት የጸና ልባዊ ፍቅር ሊኖራቸው ይገባል።

**፱ኛ** ዘጠነኛው መመሪያ ሚስት ለባሏ ውስጣዊ መልካምነትን ማድረግ እንዳለባት የሚያሳይ ነው። ለሴት በስጋዊ ጌጥ ከማጌጥ ይልቅ ለባሏ መታዘዝ፣ ባሏን በመፍራት፣ በመውደድ፣ ጌታዬ እያለች በመጥራት ሳትፈራና ሳታፍር መልካም ስራ በመስራት ንጹህ ልቦናዋን ገልጣ እያሳየች በትህትና፣ በመንፈሳውዊ ኃይል በመገዛት ብታጌጥ ይበልጥባታል። ወንድም የምድር ሀብትና ክብር ብቻ ሳትሆን የሰማይ ህይወትና ክብር ተሳታፊው ስለሆነች ሚስቱን ሳይንቅ እንደ ዓይኑ ብሌን ይጠብቃት። ባልና ሚስት አንድ ልብ አንድ አፍ ሆነው በመተማመን መኖር ይገባቸዋል እንጂ በሐሳብ መለያየት፣ መተማማት የለባቸውም። ሊቀ ሐዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስ በመልእክቱ እንዲህ ሲል ጽፏል። እንዲሁም፥ እናንተ ሚስቶች ሆይ፥ ከባሎቻችሁ አንዳንዱ ለትምህርት የማይታዘዙ ቢኖሩ፥ በፍርሃት ያለውን

ንጹሑን ኑሮአችሁን እየተመለከቱ ያለ ትምህርት በሚስቶቻቸው ኑሮ እንዲገኙ ተገዙላቸው። ለእናንተም ጠጉርን በመሸረብና ወርቅን በማንጠልጠል ወይም ልብስን በመጎናጸፍ በውጭ የሆነ ሽልማት አይሁንላችሁ። የልብ ሰዎች ሁኑ።እንዲህ በቀድሞ ዘመን በእግዚአብሔር ተስፋ ያደረጉት ቅዱሳት ሴቶች ደግሞ፣ ለባሎቻቸው ሲገዙ ተሸልመው ነበርና። እንዲሁም ሣራ አብርሃምን ትታዘዘው ጌታየም ትለው እንደነበር እናንተም ልጆቿ በበጎ ስራ ፍጹማን ሁኑ። እንዲሁም ወንዶች ሚስቶቻችሁን አክብሩ ፩ ኛጴጥ ፫፡፩-፱

**፲ኛ** ባልና ሚስት በሞት ካልሆነ በስተቀር መለያየት የለባቸውም። በሞት መለያየት ቢደርስባቸው ግን ወደ ኋላ የቀረው ንጽህናውን ጠብቆ ወይም ጠብቃ መኖር አለባቸው። በንጽሕና መኖር የማይቻላቸው ከሆነ ግን ሁለተኛ ማግባት ይችላሉ። ሴት ባሏ በሕይወት ሳለ በሕግ የጸናች ናት። ባሏ የሞተ እንደሆነ ግን ለባሏ ከገባችለት ቃል ኪዳን ነጻ ናት። ባሏ በሕይወት ሳለ ከሌላ ወንድ ብትደርስ ዝሙት ይሆንባታል። ባሏ የሞተ እንደሆነ ግን ሌላ ብታገባ ዝሙት አይሆንባትም ሰሰነችም አትባልም። ሲል ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስም በመልክቱ ጽፏል። ሮሜ ፯፡፪

**፲፩ኛ** ይህ አስራ አንደኛው ሕግ ስለ ጊዜያዊ ግጭት የሚናገር ነው። ባልና ሚስት በተለያዩ ምክንያት ሊጋጩና በመካከላቸው አለመግባባት ሊፈጠር ይችላል። ታዲያ ይህ ችግር ቢከሰትባቸው እራሳቸው ቁጭ ብለው በመንፈሳዊ እሕትና ወንድማዊ ፍቅር በውይይት መፍታት አለባቸው። ይህ ካልሆነ ግን ጉዳዩን ማንም ሳይሰማው ጉዳዩን ወደ ንስሐ አባታቸው በመውሰድ አበ ነፍሱም መክሮና ገስጾ ይፈታዋል። ከዚህ ውጭ የሆነ አካል መፍትሔ ሊሆን አይችልም። ይባስ ነገሩን በማሳደግና በማስፋት ለበለጠ አደጋ ሊዳርግ ይችላልና። መንፈሳውያን ክርስቲያኖች ይህ ችግር ቢገጥማቸው ለካህን እንጂ ለማንም መንገር የለባቸውም። ምክንያቱ ባልንጀራ ሁሉ መልካም አይደለምና፣ መልካም ጓደኛ እንዳለ ሁሉ ክፉም ይኖራል። ክፉ ባልንጀራ ደግሞ መልካሙን አመል ያጠፋል። ክፉ ባልንጀራ ጉዳዩን በምስጢር ከመያዝ ይልቅ ምስጢራቸውን እያወራ ችግራቸው እንዲሰፋ እንዲሰፋ በማድረግ ለባሰ ችግር ይዳርጋል እንጂ ምንም መፍትሔ አይሆንም። ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ ሚስት በጊዜያዊ ጠብ አትለይ፥ ብትለይ ግን ሳታገባ ትኑር ወይም ከባልዋ ትታረቅ፥ ባልም ሚስቱን አይተዋት ብዬ የተጋቡትን አዛቸዋለሁ፥ እኔ ግን አላዝም፥ ጌታ እንጂ በማለት ትዕዛዘ እግዚአብሔር መሆኑን አስተምሯል። ፩ ቆሮንቶስ ፯፡-፲

**፲፪ኛ** ይህ አስራ ሁለተኛውና የመጨረሻው ሕግ ስለ ዝምድና እና ጋብቻ ይናገራል። ዘመድ በሁለት ይከፈላል እሱም ሥጋዊ ዝምድና እና መንፈሳዊ ዝምድና ናቸው። መንፈሳዊ ዝምድና በሃይማኖት የተዛመዱ ናቸው።ለምሳሌ እንደ አበ ልጅ፣ የክርስትና አባት ወይም ናት፣ የጡት አባትና እናት ሆነን

እንድናሳድጋቸው ከእግዚአብሔር የተቀበልናቸውና የመሳሰሉት መንፈሳዊ ቤተሰብ ናቸው። ከእነሱ ጋር መጋባት አይፈቀድም።

በሥጋዊ ዝምድና ደግሞ እስከ ሰባት ትውልድ መጋባት ክልክል ነው። የሚከለከለውም ከዚህ ቀጥሎ በተጻፈው ልክ ነው።

- ወደላይ ልጅ ያባቱንና የአያቱን የቅድም አያቱን ሚስት ልጅዋን ፤ እኅቷን እናቷን በቤትም በውጭም የተወለዱ አያገባም።
- ወደታች አባት ልጁን፣ የልጅ ልጁን፤ የልጅ ልጁን የልጅ ልጅ ሚስት፤ ልጅዋን እኅቷን ፤ እናቷንና አያቷንም አያገባም።
- የወንድምና የእኅት፣የአክስትና የአጎት፣ የአማትና የምራት፣ የዋርሳና የአይት እነዚህ ሁሉ ዘመድ ናቸውና ከመጋባት ይከለከላሉ እንደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖትም እንደባህልም የዝምድና ጋብቻ አይፈቀድም። ዘሌዋ ፲፰÷፮

## ማጠቃለያ

የጋብቻ መሰረታዊ አላማ መረዳዳት፣ መተጋገዝ እንደሆነ ከላይ አይተነዋል። **ዘይቤ እግዚአብሔር ኢኮነ ሰናየ ለእጓለ እመሕያው ከመ ይንበር ባሕቲቱ አላ ንግበር ሎቱ ቢጸ ዘይረድኦ** እግዚአብሔር አምላክም አለ፡- ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም፤ የሚመቸውን ረዳት እንፍጠርለት። ዘፍ ፪÷፲፰ በማለት የብቸኝነት ጉድለት የሚያስከትለውን ፈተና እና በዚህች ዓለም የረዳት አስፈላጊነት ሰፊ በመሆኑ ጌታ ረዳት እንፍጠርለት ባለው አምላካዊ ቃል መረዳት ይቻላል የባልና የሚስት ዋና ተግባር መረዳዳት ነው። አንድ አንድ ጊዜ ሰዎች ሴቶችን የበታች ወይም የቤት ሰራተኛ አድርገው ያስባሉ። በተለይ በሀገራችን የገጠሩ ክፍል ማንኛውንም የቤት ሥራ የእናቶች ተደርጎ ይታመናል። ነገር ግን በመጽሐፍ ቅዱስ ሲመዘን የእውነት ክፍተት አለበት። ምክንያቱም መጽሐፉ እያለ ያለው የምትረዳው እንፍጠርለት ነው። ይህ ማለት አንድ እየሰራ ያለ ግለሰብ እገዛ እንደሚያስፈልገው አይነት ማለት ነው። ሰው በዚህች ምድር ሲኖር የምታግዘው፣ የምትረዳው፣የምታጽናናው፣ የችግሩ ተካፋይ በሐዘንም በደስታም ከጎኑ የምትሆን ማለት እንጂ እንደ ሰራተኛ የምታገለግለው ማለት እንዳልሆነ ሊሰመርበት ይገባል። ባልና ሚስት እርስ በርሳቸው በመረዳዳትና በመደጋገፍ ካልሆነ የዚህን ዓለም ውጣውረድ መሸከም አይችሉም። ቅድስት ሥላሴ የምትረዳው እንፈጠርለት ማለታቸው ዓለም በተናጠል የማትገፋ ዳገት በመሆኗ ነው። ስለዚህ ባሎች ሚስቶቻቸውን እንደ ረዳት እንጂ እንደ አገልጋይ መመልከት የለባቸውም። ባል ለሚስቱ አካሉ ናትና ልዩ ፍቅርና ልዩ ክብር ሊኖረው ይገባል። ሚስትም ለባሏ ልዩ ፍቅርና ልዩ አክብሮት ሊኖራት ይገባል። በዚህም ከላይ በመግቢያው

እንደጠቀስነው መልካም ዛፍ መልካም ፍሬ ያፈራል ከመልካም ትዳር መልክም ልጆች ይወለዳሉ። መልካም ልጆች የመልካም ትዳር ፍሬዎች ናቸው።

ሚስት ማግባት፣ ባል ማግኘት እንዲሁም ጋብቻ መፈጸም ቀላል ነው። ትዳርን አክብሮ ያለነቀፋ መኖር ግን የብዙዎች ተጋድሎ ሆኖ ይታያል። በዓለም ውስጥ የሚኖሩ ባለትዳሮች በተለያየ ምክንያት ጋብቻቸው ይፈተናል። በተለይ ልጅ ባለማግኘት የሚመጣ ፈተና እስከመለያየት ሲያደርስ እናያለን። ነገር ግን መፍትሔው መለያየት ሳይሆን ልጆች የእግዚአብሔር ስጦታ መሆናቸውን አምኖ በእምነት፣ በተስፋ፣ በፍቅር ጸንቶ መኖር ይገባል። እግዚአብሔርን ተስፋ ማድረግ አማራጭ የሌለው መፍትሔ ነው። የቀደሙ አበው ቅዱሳን ታሪክ የሚያሳየው ያንን ነው። ለምሳሌ  ከሴቶች ከተወለዱት መካከል የሚያክለው የለም። ተብሎ በጌታ **የተመሰከረለት፣ስመ ትርጓሜሁ ፍስሐ ወሰላም የተባለው** መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ የመልካም ዛፎች ፍሬ በጽናትና በቅድስና የተገኘ በረከት ነበር። ቅድስት ኤልሳቤጥና ካህኑ ዘካርያስ በተቀደሰው ትዳር ጸንተው የኖሩ ቅዱሳን እንደነበሩ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ሲል ይገልጻቸዋል ።ሁለቱም በጌታ ትእዛዝና ሕግጋት ሁሉ ያለ ነቀፋ እየሄዱ በእግዚአብሔር ፊት ጻድቃን ነበሩ።ሉቃ ፩፥፮ ሰዎች በጌታ ትዕዛዝና ሕግጋት ቢኖሩ በእግዚአብሔር ፊት ሞገስ ያገኛሉ። በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የሚኖሩ አማኞች ይህንን መንፈሳዊ መመሪያ አክብረው ቢኖሩ  በሁለት መንገድ ተጠቃሚዎች ይሆናሉ።በነፍስም በሥጋም። እንዲሁም ለሚወልዷቸው ልጆች ቢያስተምሯቸው መጠነ ሰፊ ሃይማኖታዊና መንፈሳዊ ትርፍ ያተርፋሉ። ልጆች ከሚሰሙትና ከሚነገራቸው ይልቅ የሚያዩትን ይፈጽማሉና።

**ስብሐት ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ዱ አምላክ ለዘዐልዓለኒ ከመ እጽሕፍ ዘንተ ጦማረ፣** ምስጋና ይሁን አነሳስቶ ለአስጀመረኝ አስጀምሮ ለአስፈጸመኝ አንድ አምላክ ለሆነ ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ አሜን።

መልአከ ሰላም ቀሲስ ሰሎሞን ኃይሌ ልዮን ፈረንሳይ